www.abyssinialaw.com

# የተሻሻለው የኦሮሚያ ክልል ሕገ-መንግስት

(1994)

www.abyssinialaw.com



# የተሻሻለው የ1994 ዓ.ም የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ

በክልሉ ነዋሪ ሕዝብ ተወካዮች ተመክሮበት ሰኔ 14 ቀን 1987 ዓ.ም በመጀመሪያ የፀደቀውን እና እስካሁን ሲሰራበት የቆየውን የክልሉን ሕገ መንግሥት በጥልቀት ተመልክቶ፣ በተለይም የክልሉን መንግሥት አካላት የሥልጣን ክፍፍልንና ተጠያቂነትን በግልፅ መደንገግና ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት መስጠት በሚያስችልበት ሁኔታ ሕገ መንግሥቱን ማሻሻል ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

በሥራ ላይ ባለው የክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 49 (3) (ሀ) እና 93 መሠረት ከዚህ የሚከተለው የተሻሻለው የ1994 ዓ.ም የክልሉ ሕገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ ታውጇል።

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የ1994 ዓ.ም የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር 46/1994" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. የተሻሻለው የ1994 ሕገ መንግሥት ስለመፅደቁ

በአዋጅ ቁጥር /1987 ዓ.ም የፀደቀው የክልሉ ሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች ይዘቱና አተማመር ከታዩ በኋላ የተሻሻለው የ1994 ዓ.ም የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግሥት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

www.abyssinialaw.com

3. ስለነባር ሕጎች ተፈፃሚነት

በሥራ ላይ ያለ ማንኛውም ነባር ሕግ ከተሻሻለው ሕገ መንግሥት ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈፃሚነቱ ይቀጥላል።

4. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ማዕደቂያ አዋጅ ከተሻሻለው ሕገ መንግሥት ጋር ከጥቅምት 17 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዳማ፣ ጥቅምት 17 ቀን 1994 ዓ.ም

ሱፊያን አህመድ
የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት
ምክትል ፕሬዚዳንት

www.abyssinialaw.com

# የተሻሻለው የ1994 ዓ.ም የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግሥት

እኛ የኦሮሞ ህዝብ በእኛና በሌሎች የአገሪቱ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ላይ ተንሰራፍቶ የነበረው የጭቆና ሥርዓት ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻችንን አፍኖ፣ በተዛቡ ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች በመተብተብ ለድህነትና ለኋላ ቀርነት ዳርጎን በገዛ ሀገራችን እንደ ሁለተኛ ዜጋ በመቁጠር የሰቆቃ ኑሮ እንድናሳልፍ ማድረጉን በመቃወምና በማያዳግም ሁኔታም መቃረም እንዳለበት በማመን ሥርዓቱን ገርስሰን የጣልን በመሆኑ፣

ሥርዓቱ ከተገረሰሰ በኋላ በአገራችን የግለሰቦችና የመላው ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት መገንጠልን ጨምሮ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በሙሉ የተከበሩበትና በአጠቃላይ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት የፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሥርዓት መገንባት የሚሰጠንን ጠቀሜታ በመገንዘብ ሕገ መንግሥታችንን በጋራ ያፀደቅን በመሆኑ፣

እኛም የኦሮሞ ሕዝብ ለተፋጠነ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት፣ ለዘላቂ ሰላምና ለዳበረ ዲሞክራሲ የምንበቃው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት መሠረት ያደረገ፣ ከክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገነዘበና ሕገ መንግሥታዊ መብቶቻችንን ባልተሸራረፈ ሁኔታ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ሕገ መንግሥት ሲኖረን መሆኑን በማመን ከመካከላችን መርጠን በላክናቸው ተወካዮች አማካይነት እስከ አሁን ሀንዮ ሥራ ላይ ያለውን ሕገ መንግሥት ሰኔ 15 ቀን 1987 ዓ.ም ማስደቃችንን እያስታወስን፣

www.abyssinialaw.com

ድሮው በሥራ ላይ ያለው ሕገ መንግሥት የመንግሥት የሥልጣን ክፍፍልና የእርስ በርስ ቁጥጥርና መርህን በሚከተል የአሠራር ግልፅነትንና የሕዝብ ተሳትፎን በሚያጎለብት፣ ተጠያቂ የሆነና ብቃት ያለውን የመንግሥት አደረጃጀት በሚያሣይ የሕዝብ ተሳትፎን በተሻለ ሁኔታ በሚያረጋግጥና አገራችንና ክልላችን ከሚገኙበት ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተገናዘበ መልኩ ተሻሽሎ መውጣት ያለበት መሆኑን በማመን፣

እነሆ ዛሬ ጥቅምት 17 ቀን 1994 ዓ.ም በአዳማ ከተማ ባካሄድነው የክልሉ ጨፌ አስቸኳይ ጉባኤ የቀረበውን የተሻሻለ ሕገ መንግሥት መክረንበትና በዝርዝር ተወያይተንበት በአብላጫ ድምፅ አፅድቀነዋል።

www.abyssinialaw.com

# ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1

### የክልሉ መንግሥት ስያሜ

" የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት " ተብሎ የሚጠራ ዲሞክራሲያዊ መዋቅር ያለው መንግስት በዚህ ሕገ መንግሥት ተመሥርቷል።

### አንቀጽ 2

### የኦሮሚያ ክልል ወሰን

1. የኦሮሚያ ክልል የኦሮሞ ሕዝብና ሌሎች በኦሮሚያ ውስጥ ለመኖር የመረጡ ሕዝቦች የሰፈሩበት የተያያዘ መልክአምድር ሆኖ፣

   በሰሜን - ከአፋርና ከአማራ ክልሎች፣
   በደቡብ - ከደቡብ ብሔር- ብረሰቦችና ሕዝቦች ክልልና ከኬንያ፣
   በምስራቅ - ከሱማሌ ክልልና
   በምዕራብ - ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ ከጋምቤላ ክልልና ከሱዳን

   የሚዋሰን ነው።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የኦሮሚያ ክልል ከሌሎች አጐራባች ክልሎች ጋር ያለው ወሰን የሕዝቦችን ፍላጐት መሠረት በማድረግ ከሚመለከተው ክልል ጋር በሚደረግ ስምምነት ሊለወጥ ይችላል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ስምምነት ላይ መድረስ ካልተቻለ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 48 በሚደነግገው መሠረት በፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚወሰን ይሆናል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 3
## ሰንደቅ ዓላማና አርማ

1. የኦሮሚያ ክልል ሰንደቅ ዓላማና አርማ የክልሉን ሕዝብ ማንነት፣ ሉአላዊነት፣ አንድነት፣ ብሔራዊ ኩራት፣ ጀግንነትና ታሪክ እንዲሁም የኢኮኖሚ ትስስር የሚያንፀባርቅ ይሆናል። የክልሉ ሰንደቅ ዓላማ ከላይ ቀይ፣ ከመሃል ነጭ፣ ከታች ጥቁር ሆኖ በመሃሉ የኦዳ ምልክት ይኖረዋል።

2. የክልሉ አርማ በውስጡ የዋርካ፣ የስንዴ ዘለላና የፋብሪካ ጊር ምልክት ይኖረዋል።

3. የሰንደቅ ዓላማውና የአርማው ዝርዝር በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 4
## መዝሙር

የኦሮሚያ ክልል የኦሮሞን ሕዝብ የረዥም ዘመን የጀግንነትና የፍትሕ ታሪክ እንዲሁም የተገኘውን ድል የሚያሳይና ለተሻለ ኑሮ ያለውን ምኞት የሚያንፀባርቅ የራሱ መዝሙር ይኖረዋል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 5
## የሥራ ቋንቋ

ኦሮምኛ የክልሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ ይሆናል፤ የሚጻፈውም በላቲን ፊደል ነው።

## አንቀጽ 6
## ርዕሰ ከተማ

የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ ከተማ አዳማ ነው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 7
## የጾታ አገላለጽ

በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው እንደአግባብነቱ የሴት ፆታንም ያካትታል።

# ምዕራፍ ሁለት
# የሕገ መንግስቱ መሠረታዊ መርሆዎች

## አንቀጽ 8
## የህዝቡ የሥልጣን ባለቤትነት

የኦሮሞ ሕዝብ የክልሉ የበላይ ሥልጣን ባለቤት ሲሆን፣ የህዝቡ የበላይነትም የሚገለጸው በሚመርጣቸው ተወካዮችና ራሱ በቀጥታ በሚያደርገው ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ነው።

## አንቀጽ 9
## የህገ መንግሥት የበላይነት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ህገ መንግስት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. ይህ ሕገ መንግስት የክልሉ የበላይ ህግ ነው። ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር ወይም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይረውም፤

2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ፣ የመንግስት አካል፣ የፖለቲካ ድርጅት ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለስልጣኖቻቸው ይህን ህገ መንግስት የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው።

3. በዚህ ሕገ መንግስት ከተደነገገው ውጪ በማናቸውም አኳኋን የመንግስት ስልጣን መያዝ የተከለከለ ነው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 10
## ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች

1. ሰብአዊ መብቶችና ነጻነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ፣ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው።

2. የግለሰቦችና የሕዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩ ናቸው።

## አንቀጽ 11
## የመንግሥትና የሀይማኖት መለያየት

1. መንግሥትና ሀይማኖት የተለያዩ ናቸው።

2. መንግስታዊ ሀይማኖት አይኖርም።

3. መንግስት በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፤ ሀይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም።

## አንቀጽ 12
## የመንግስት አሠራርና ተጠያቂነት

1. የክልሉ መንግስት አሠራር ለህዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት።

2. ሕዝቡ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ሊያነሳው ይችላል፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

3. ማንኛውም የሥራ ሃላፊ ወይም የሕዝብ ተመራጭ ሃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል

www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ ሶስት

## መሠረታዊ መብቶችና ነጻነቶች

### አንቀጽ 13

### ተፈጻሚነትና አተረጓጐም

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ መንግስት የህግ አውጪ፣ የህግ አስፈጻሚና የዳኝነት አካሎች በዚህ ምዕራፍ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው።

2. በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት መሠረታዊ መብቶችና ነጻነቶች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሕግጋት፣ ከአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችና ከሌሎች አለም አቀፍ ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጐማሉ።

## ክፍል አንድ

## ሰብአዊ መብቶች

### አንቀጽ 14

### የሕይወት ፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት

ማንኛውም ሰው ሰብአዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነት መብትና ነጻነት አለው።

### አንቀጽ 15

### በሕይወት የመኖር መብት

ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው። ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም።

www.abyssinialaw.com

## <u>አንቀጽ</u> 16

## <u>የአካል ደህንነት መብት</u>

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው።

## <u>አንቀጽ</u> 17

## <u>የነጻነት መብት</u>

1. በሕግ ከተደነገገው ስርአት ውጭ ማንኛውም ሰው ነጻነቱን አያጣም።

2. ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርአት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም።

## <u>አንቀጽ</u> 18

## <u>ኢ - ሰብአዊ አያያዝ ስለመከልከሉ</u>

1. ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት ኢሰብአዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው።

2. ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም። ለማንኛውም አላማና ሁኔታ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነው።

3. ማንኛውም ሰው በሃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት ማንኛውንም ሥራ እንዲሠራ ማድረግ የተከለከለ ነው።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) "በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ማሟላት" የሚለው ሀረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም፡

www.abyssinialaw.com

ሀ) [illegible] በጦርነት ወይም በአስቸኳይ ጊዜ የሚሰራውን ማንኛውም ሥራ፣

ለ) ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ህሊናው የማይፈቅድለት ሰው በምትኩ የሚሰጠው አገልግሎት፣

ሐ) የማህበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥን ማንኛውም አገልግሎት፣

መ) በሚመለከተው ሕዝብ ፈቃድ በአካባቢው የሚፈጸምን ማንኛውም የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ልማት ሥራ።

## አንቀጽ 19

## የተያዘ ሰው መብት

1. ማንኛውም ሰው ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በሚያዝበት ጊዜ የቀረበበት ክስና የተያዘበት ምክንያት በሚገባው ቋንቋ ወዲያውኑ ይነገረዋል።

2. የተያዘ ሰው የተከሰሰበትን ጉዳይ በተመለከተ ያለመናገር መብት ያለው መሆኑ፣ ለመናገር ከመረጠ ደግሞ የሚሰጠው ቃል በፍርድ ቤት በራሱ ላይ በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል መረዳት በሚችለው ቋንቋ እንዲተያዘ ወዲያውኑ ይገለጽለታል።

3. ማንኛውም የተያዘ ሰው በተያዘ በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አለው፤ ይህም ጊዜ [illegible]

www.abyssinialaw.com

4. ማንኛውም የያዘው አካል ወይም የሕግ አስከባሪ በጊዜ ገደቡ መሠረት ፍርድ ቤት በማቅረብ የተያዘበትን ምክንያት ካላስረዳ ፍርድ ቤቱ የአካል ነፃነቱን እንዲያስከብርለት መጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አለው። ሆኖም ፍትህ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፣ ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰው በጥበቃ ሥር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ ሲጠየቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቅድ ይችላል። ፍርድ ቤቱ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ የሚወስነው ሃላፊ የሆኑት ህግ አስከባሪ ባለስልጣኖች ምርመራውን አጣርተው የተያዘው ሰው በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያለውን መብት በሚያስከብር መልኩ መሆን አለበት።

5. ማንኛውም ሰው በራሱ ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጥ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያመጣ አይገደድም። በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም።

6. የተያዘ ሰው በዋስ የመፈታት መብት አለው። ሆኖም በህግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች መሠረት ፍርድ ቤቱ ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፈታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል።

## አንቀጽ 20
## የተከሰሰ ሰው መብት

1. የተከሰሰ ሰው ክስ ከቀረበበት በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አለው። ሆኖም የተከራካሪዎችን የግል ሕይወት፣ የሕዝቡን የሞራል ሁኔታ ወይም የአገሪቱን ወይም የክልሉን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል።

2. የተከሰሰ ሰው ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገረውና ክሱን በጽሁፍ የማግኘት መብት አለው።

www.abyssinialaw.com

3. ማንኛውም ተከሣሽ በፍርድ ሂደት ጊዜ በተከሰሰበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት አለው። በምስክርነት እንዲቀርብም ያለመገደድ መብት አለው።

4. የተከሰሰ ሰው የቀረበበትን ማንኛውም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡበትን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችለውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቹ ቀርበው እንዲሰሙለት የመጠየቅ መብት አለው።

5. የተከሰሰ ሰው በመረጠው የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም ከሌለውና ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ካጋጠመ ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አለው።

6. ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠበት ትእዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ተከሣሹ ቅሬታ ካለው ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል።

7. ተከሳሽ የፍርዱ ሂደት በማይገባው ቋንቋ በሚካሄድበት ጊዜ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጐምለት የመጠየቅ መብት አለው።

## አንቀጽ 21

## በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሰረ ሰው መብት

1. በጥበቃ ሥር ያለ ወይም በፍርድ የታሰረ ሰው ሰብአዊ ክብሩን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አለው።

2. ማንኛውም የታሰረ ሰው ከትዳር ጓደኛው፣ ከቅርብ ዘመዶቹ፣ ከጓደኞቹ ፣ ከሃይማኖት አማካሪዎቹ ፣ ከሃኪሞቹና ከሕግ አማካሪዎቹ ጋር ለመገናኘትና እንዲጐበኙት እድል የማግኘት መብት አለው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 22

## የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ

1. ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በህግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም። እንዲሁም ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ ከነበረው የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም ሰው ላይ አይወሰንም።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም፣ ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የወጣ ህግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣው ሕግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## አንቀጽ 23

## በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ህግና ሥነ ስርአት ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ህጎች መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም።

## አንቀጽ 24

## የክብርና የመልካም ስም መብት

1. ማንኛውም ሰው በማንኛውም ሥፍራ በሰብአዊ ፍጡርነቱ እውቅና የማግኘት መብት አለው።

2. ማንኛውም ሰው ሰብአዊ ክብሩና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለው።

3. ማንኛውም ሰው የራሱን ስብእና ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነጻ የማሳደግ መብት አለው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 25
## የእኩልነት መብት

ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው። በመካከላቸው ማንኛውም አይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር/ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው።

## አንቀጽ 26
## የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት

1. ማንኛውም ሰው የግል ህይወቱና ግላዊነቱ የመከበር መብት አለው። ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ፣ ሰውነቱና ንብረቱ ከመበርበር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል።

2. ማንኛውም ሰው በግል የሚጽፋቸውና የሚጻጻፍባቸው፣ በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች፣ እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም።

3. የመንግስት ባለስልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው። አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነት፣ የሕዝቡን ሰላም ለመጠበቅ፣ ወንጀል ለመከላከል፣ ጤናንና የህዝብን የሞራል ሁኔታ ለመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነጻነት ለማስከበር አላማዎች በወጡ ህጎች መሠረት ካልሆነ በስተቀር የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 27

## የሀይማኖት ፣ የሕሊናና የእምነት ነጻነት

1. ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የሀሊና እና የሃይማኖት ነጻነት አለው። ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሀይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለጽ መብትን ያካትታል።

2. በፌዴራል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 90 (2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችሏቸው የሃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ።
3. ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነጻነት በሀይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም።

4. ወላጆችና ሌሎች ሕጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸው መሠረት የሀይማኖታቸውንና የመልካም ሥነ ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው።

5. ሀይማኖትንና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለው የሕዝቡን ደህንነት፣ ሰላምን፣ ጤናን፣ ትምህርትን፣ የሕዝብን የሞራል ሁኔታ ፣ የሌሎች ዜጎችን መሠረታዊ መብቶችና ነጻነቶች መንግስት ከሃይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ሕጎች ይሆናል።

## አንቀጽ 28

## በሰብእና ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች

ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የአገሪቱ ሕጎች በሰው ልጆች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች የሰው ዘር የማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ፣ በአስገዳጅ ሁኔታ ሰውን

www.abyssinialaw.com

የመሰወር ወይም ኢሰብአዊ የድብደባ ድርጊቶች በፈጸሙት ሰዎች ላይ ክስ ማቅረቢ በይርጋ አይታገድም። ይህ ወንጀል በህግ አውጪው አካል ወይም በማንኛውም ሌላ የመንግስት አካል ውሳኔዎች በምህረት ወይም በይቅርታ አይታለፍም።

## ክፍል ሁለት

## ዴሞክራሲያዊ መብቶች

### አንቀጽ 29

### የአመለካከት፣ሃሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት

1. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል።

2. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሃሳቡን የመግለጽ ነጻነት አለው። ይህ ነጻነት በክልሉ ውስጥም ሆነ ከክልሉ ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሁፍ ወይም በህትመት፣ በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሃሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነጻነቶች ያካትታል።

3. የፕሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙሀን እንዲሁም የሥነ ጥበብ ፈጠራ ነጻነት ተረጋግጧል። የፕሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል፣

   ሀ) የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን፣
   
   ለ) የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት እድልን።

4. ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ ሃሳቦችና አመለካከቶች በነጻ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ፕሬስ በተቋምነቱ የአሠራር ነጻነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የህግ ጥበቃ ይደረግለታል።

www.abyssinialaw.com

5. በክልሉ መንግሥት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመንግስት ቁጥጥር ሥር ያለ መገናኛ ብዙሀን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል።

6. እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው የሀሳብና መረጃ የማግኘት ነጻነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመስርተው በሚወጡ ህጐች ብቻ ይሆናል። የወጣቶች ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ህጋዊ ገደቦች በእነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ። የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በህግ የሚከለከሉ ይሆናሉ።

7. ማንኛውም ሰው ከላይ በተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ሕጋዊ ገደቦችን ጥሶ ከተገኘ በህግ ተጠያቂ ይሆናል።

## አንቀጽ 30
## የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት

1. ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው። ከቤት ውጭ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶችንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ሥርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ።

2. ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ፣ የጦርነት ቅስቀሣዎችን እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ህጐች መሠረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 31
## የመደራጀት መብት

ማንኛውም ሰው ለማንኛውም አላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለው። ሆኖም አግባብ ያለውን ህግ በመጣስ ወይም ህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በህገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 32
## የመዘዋወር ነፃነት

በፌዴራል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 32 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ ወይም በህጋዊ መንገድ በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ሰው በፈለገው የክልሉ አካባቢ የመዘዋወር፣ የመኖሪያ ቦታ የመመስረት፣ ሥርቶ የመኖር፣ ሀብት የማፍራትና የመያዝ እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ክልሉን የመልቀቅ ነፃነት አለው።

## አንቀጽ 33
## በመንግሥታዊና ሕዝባዊ ሥራዎች የመሳተፍ መብት

በክልሉ ውስጥ ነዋሪ የሆነና የክልሉን የሥራ ቋንቋ የሚያውቅ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በማንኛውም የክልሉ መንግሥታዊ ወይም ሕዝባዊ ሥራ ተመርጦ ወይም ተቀጥሮ የመሥራት መብት አለው።

## አንቀጽ 34
## የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች

1. በህግ የተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሔር/ብሔረሰብ ወይም በሃይማኖት ወይም በሌላ ምክንያት ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመሥረት መብት አላቸው። በጋብቻ አፈጻጸም፣ በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው። በፍቺ ጊዜ የልጆችን መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ሕጎች ይወጣሉ።

www.abyssinialaw.com

2. ጋብቻ በተጋቢዎች ነጻና ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ ብቻ ይመሰረታል።

3. ቤተሰብ የህብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ ነው፤ ከህብረተሰብና ከመንግስት ጥበቃ ያገኛል።

4. በህግ በተለይ በሚዘረዘረው መሠረት በሃይማኖት ወይም በባህላዊ ሥርዓቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈጸሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ህግ ሊወጣ ይችላል።

5. ይህ ህገ መንግሥት የግልና የቤተሰብ ህግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖታዊ ወይም በባህላዊ ሥርዓት መሠረት መዳኘትን አይከለክልም። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 35
## የሴቶች መብቶች

1. ሴቶች ይህ ህገ መንግስት ባረጋገጠላቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው።

2. ሴቶች በዚህ ሕገ መንግስት በተደነገገው መሠረት በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው።

3. ሴቶች በበታችነትና በልዩነት ሲታዩ በመቆየታቸው ምክንያት የደረሰባቸውን የታሪክ ጠባሳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ጠባሳ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ ርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው። ከዚህ አኳያ የሚወሰዱት እርምጃዎች አላማ በፖለቲካዊ፣ በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግስትና በግል ተቋሞች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ታሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው።

www.abyssinialaw.com

4. ሴቶች ከጐጂ ልማድ ተጽዕኖ ለመላቀቅ ያላቸውን መብት መንግሥት ማስከበር አለበት። ሴቶችን የሚጐዱ ወይም በአካላቸው ወይም በአእምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጐች፣ ወጐችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው።

5. ሴቶች የቅጥር፣ የሥራ ዕድገት፣ የእኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው።

6. በመንግሥት ወይም በግል ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ ሴቶች፦

   ሀ) የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ ደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸው። የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሰራውን ሥራ ሁኔታ፣ የሴቷን ጤንነት፣ የህፃኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በህግ ይወሰናል፤

   ለ) የወሊድ ፍቃድ በህግ በሚወሰነው መሠረት ከሙሉ ደመወዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፍቃድን ሊጨምር ይችላል።

7. ሴቶች በእርግዝና ወይም በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት፣ መረጃና አቅም የማግኘት መብት አላቸው።

8. ሴቶች በክልሉ የልማት ፖሊሲዎች፣ እቅድና በፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈጻጸም፣ በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ላይ ሃሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው።

9. ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው። በተለይ መሬትን በመጠቀም፣ የመሬት ይዞታን በማስተላለፍ፣ በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው። እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 36
## የህፃናት መብቶች

1. ማንኛውም ህፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት፣

   ሀ) በሕይወት የመኖር፣

   ለ) ስምና ዜግነት የማግኘት፣

   ሐ) ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅ የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፣

   መ) ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርት፣ በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎችን እንዲሠራ ያለመገደድ ወይም ከመስራት የመጠበቅ፣

   ሠ) በትምህርት ቤቶች ወይም በህፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች በአካሉ ላይ ከሚፈጸም ወይም ከጭካኔና ኢሰብአዊ ከሆነ ቅጣት ነፃ የመሆን።

2. ህፃናትን የሚመለከቱ ርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግስታዊ ወይም በግል በጐ አድራጐት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች ፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በህግ አውጪ አካላት የህፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት።

3. ወጣት አጥፊዎች፣ በማረሚያ ወይም በማቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ፣ በመንግስት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች፣በመንግስት ወይም በግል እጓለማውታን ተቋሞች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው።

4. ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ህፃናት በጋብቻ ውስጥ ከተወለዱ ህፃናት ጋር እኩል መብት አላቸው።

5. መንግሥት ለእጓለማውታን ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል። በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ፣ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሠረቱ ያበረታታል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 37
## ፍትህ የማግኘት መብት

1. ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የመዳኘት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ውሳኔ ወይም ፍርድ፣

   ሀ) ማንኛውም ማህበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፣

   ለ) ማንኛውንም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው።

## አንቀጽ 38
## የመምረጥና የመመረጥ መብት

1. ማንኛውም የክልሉ ሕዝብ በዘር፣ በቀለም፣ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሀይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሠረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፣

   ሀ) በቀጥታና በነጻነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካይነት በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ፣

   ለ) በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 33 የተካፈው እንደተጠበቀ ሆኖ እድሜው 18 ዓመት ሲሞላ በህግ መሠረት የመምረጥ፣ 21 ዓመት ሲሞላው የመመረጥ መብት አለው።

   ሐ) በማናቸውም የመንግስት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ፣ ምርጫው ሁሉን አቀፍ፣ በሁሉም እኩልነት ላይ የተመሰረተና

www.abyssinialaw.com

መራጩ ፈቃዱን በምስጢር ድምጽ አሰጣጥ በነጻነት የሚገልጽበትና ዋስትና የሚሰጥ መሆን አለበት።

2. ማንኛውም ሰው በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በሠራተኞች፣ በንግድ፣ በአሰሪዎችና በሙያ ማኅበራት ለተሳትፎ ድርጅት የሚጠይቀውን ጠቅላላና ልዩ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ በፍላጎት አባል የመሆን መብቱ የተከበረ መሆን አለበት።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(2) በተመለከቱት ድርጅቶች ውስጥ ለሃላፊነት ቦታዎች የሚካሄዱ ምርጫዎች ነጻና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ይፈጸማሉ።

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(2) እና (3) ድንጋጌዎች የህዝብን ጥቅም ሰፋ ባለ ሁኔታ የሚነኩ እስከሆነ ድረስ በህዝባዊ ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 39

## የኦሮሞ ሕዝብ ብሔራዊ መብቶች

የኦሮሞ ሕዝብ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ህገ መንግስት የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብት በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው። በዚህ መሠረት የኦሮሞ ሕዝብ፣

1. የራሱን ብሔራዊ ማንነት የመጠበቅና የማስከበር፣ ቅርሱንና ታሪኩን የመንከባከብና የማበልፀግ እንዲሁም በቋንቋው የመጠቀም ፣ ቋንቋውን የማሳደግና ባህሉን የመግለጽ መብት አለው፣

2. በራሱ መልክአ ምድራዊ ክልል ውስጥ የራሱን ጉዳይ በራሱ የማካናወንና ራሱን የማስተዳደር እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ውስጥ በነጻነትና አድልዎ በሌለበት ተገቢና ፍትሐዊ በሆነ አግባብ ውጤታማ ተሣትፎ ለማድረግ መብት አለው፣

3. ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት፣ በሰፈረበት መልክአ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግስታዊ ተቋማት የማቋቋምና በፌዴራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብት አለው፣

www.abyssinialaw.com

4. በዚህ አንቀጽ በተራ ቁጥር (1) (2) እና (3) የተጠቀሱት መብቶች ታግደው፣ ተረገጠ፣ ወይም ተሸራረፈ ብሎ ባመነበትና እንዲህንም በአንድነት ሥር ሆኖ ሊያስተካክላቸው ባልቻለበት ጊዜ እስከመገንጠል ድረስ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብቱን ተግባራዊ ያደርጋል፡

5. የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል ድረስ ያለው መብት በሥራ ላይ የሚውለው፤

   ሀ) የመገንጠሉ ጥያቄ ባክልሉ ጨፌ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ፤

   ለ) የክልሉ ጨፌ የመገንጠል ውሳኔ በደረሰው በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የፌዴራሉ መንግስት ሕዝበ - ውሳኔ ሲያደራጅ፤

   ሐ) የመገንጠሉ ጥያቄ በህዝበ - ውሳኔው በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ፤

   መ) የፌዴራሉ መንግስት ለክልሉ ጨፌ ስልጣኑን ሲያስረክብና

   ሠ) በህግ በሚወሰነው መሠረት የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነው።

6. በዚህ ህገ መንግስት ውስጥ "የኦሮሞ ሕዝብ" ማለት ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያለው፣ የኦሮምኛ ቋንቋ የሚናገር፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና አለኝ ብሎ የሚያምንና በአብዛኛው በተያያዘ መልክአምድር የሚኖር ሕብረተሰብ ነው፤

## አንቀጽ 40
## የንብረት መብት

1. ማንኛውም ሰው የግል ንብረት ባለቤት መሆን ይችላል። ይህ መብት የህዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በህግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት

www.abyssinialaw.com

የመያዝና በንብረቱ የመጠቀም ወይም የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረቱን የመሸጥ፣ የማውረስ ወይም በሌላ መንድ የማስተላለፍ መብቶችን ያካትታል።

2. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "የግል ንብረት" ማለት ማንኛውም የክልሉና ከክልሉ ውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጣቸው አገር አቀፋዊ ወይም ክልላዊ ማኅበራት ወይም አግባብ ባላቸው ሁኔታዎች በህግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤቶች እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ማኅበረሰቦች በጉልበታቸው፣ በፈጠራ ችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤት ነው።

3. የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥ ወይም የማይለወጥ የክልሉ ህዝብ የጋራ ንብረት ነው።

4. የክልሉ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

5. በክልሉ የሚገኙ አርብቶ አደሮች ለግጦሽም ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበት መሬት በነጻ የማግኘት፣ የመጠቀምና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት አላቸው። አፈጻጸሙ በህግ ይወሰናል።

6. የመሬት ባለቤትነት የሕዝብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግስት ለግል ባለሀብቶች በህግ በሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብት ያስከብርላቸዋል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

7. ማንኛውም ሰው በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው። ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሣት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሣ ክፍያ የመጠየቅ መብትን ያካትታል። ዝርዝር አፈጻጸሙ በህግ ይወሰናል።

www.abyssinialaw.com

8. የክልሉ መንግስት ለሕዝቡ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ ይችላል።

## አንቀጽ 41
## የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶች

1. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ ወይም በክልሉ ውስጥ ለመኖር የሚፈልግ ሌላ ኢትዮጵያዊ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመስራት መብት አለው።

2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ መተዳደሪያውን፣ ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው።

3. የክልሉ ነዋሪዎች ሁሉ በመንግስት ገንዘብ በሚካሄዱ ማኅበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸው።

4. የክልሉ መንግስት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ለሕዝብ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመድባል።

5. የክልሉ መንግስት የአካልና የአእምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ህፃናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የክልሉ ኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል።

6. የክልሉ መንግስት ለሥራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል፣ እንዲሁም በሚያካሂደው የሥራ ዘርፍ ውስጥ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሥራ ፕሮግራሞችን ያወጣል፣ ፕሮጀክቶችን ያካሂዳል።

7. የክልሉ መንግስት የክልሉ ነዋሪዎች ጠቃሚ ሥራ የማግኘት እድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል።

www.abyssinialaw.com

8. ገበሬዎችና አርብቶ አደሮች በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር የሚያስችላቸውንና ለብሔራዊ ሀብት ካደረጉት የምርት አስተዋጽኦ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተገቢ ዋጋ ለምርት ውጤቶቻቸው የማግኘት መብት አላቸው። የክልሉ መንግስት የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ልማት ፖሊሲዎችን በሚተልምበት ጊዜ በዚህ አላማ መመራት አለበት።

9. መንግስት የባህልና የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብና ለሥነ ጥበብና ለስፖርት መስፋፋት አስተዋጽኦ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

## አንቀጽ 42

## የሠራተኞች መብቶች

1. ሀ) የፋብሪካና አገልግሎት ሰጭ ተቋሞች ሠራተኞች፣ ገበሬዎች፣ የእርሻ ሠራተኞች፣ ሌሎች የገጠር ሠራተኞች፣ ከተወሰነ ኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግስት ሠራተኞች የሥራና የኢኮኖሚ ሁኔታቸውን ለማሻሻል በማኅበር የመደራጀት መብት አላቸው። ይህ መብት የሠራተኛ ማኅበራትንና ሌሎች ማኅበራትን ማደራጀት ከአሠሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብትን ያካትታል፤

   ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) የተመለከቱት የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ ማቆምን ጨምሮ ቅሬታቸውን የማሰማት መብት አላቸው፤

   ሐ) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) መሠረት ዕውቅና ባገኙት መብቶች ለመጠቀም የሚችሉት የመንግስት ሠራተኞች በህግ ይወሰናሉ፤

   መ) ሴት ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።

www.abyssinialaw.com

ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ሰዓት፣ እረፍት፣ መዝናኛ ጊዜ፣ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የእረፍት ቀኖች፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት፣ እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው።

3. እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) መሠረት እውቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት ሠራተኛ ማኅበራት ስለሚቋቋሙበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋሉ።

## አንቀጽ 43

## የልማት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች አካባቢያቸውን የመጠበቅና የማልማት፣ የኑሮ ሁኔታቸውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።

2. የክልሉ ነዋሪዎች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ፣ በተለይም አባል የሆኑበትን ማኅበረሰብ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ ሃሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው።

3. የልማት እንቅስቃሴ ዋና አላማ የክልሉን ነዋሪዎች እድገትና መሠረታዊ ፍላጐቶች ማማሏት ይሆናል።

## አንቀጽ 44

## የአካባቢ ደህንነት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች ንፁህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው።

2. የክልሉ መንግስት በሚያካሂዳቸው ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ በመንግስት በቂ እርዳታ ወደሌላ አካባቢ መዘዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸው።

www.abyssinialaw.com

# ምዕራፍ አራት

# የክልሉ መንግሥት አደረጃጀትና የሥልጣን ክፍፍል

## አንቀጽ 45

## የክልሉ አስተዳደር እርከኖች

ክልሉ በክልል፣ በዞኖች፣ በወረዳዎችና በቀበሌዎች የተዋቀረ ነው። ይሁን እንጂ ጨፌ ኦሮሚያ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች የአስተዳደር እርከኖችን ሊያዋቅር ይችላል።

## አንቀጽ 46

## የክልሉ መንግሥት የሥልጣን አካላት

1. የክልሉ መንግሥት ሕግ አውጪ አካል ጨፌ ኦሮሚያ ነው፣ እሱም የክልላዊ መንግሥቱ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሆኖ ተጠሪነቱም ለወከለው ሕዝብ ነው።

2. የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈፃሚ አካል የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለጨፌ ኦሮሚያ ነው።

3. የክልሉ የዳኝነት ሥልጣን የክልሉ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው።

## አንቀጽ 47

## የክልሉ መንግሥት ሥልጣንና ተግባር

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ውስጥ በግልፅ ተለይተው ለፌዴራሉ መንግሥት ወይም ለፌዴራሉ መንግሥትና ለክልሉ መንግሥት በጋራ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውጭ ያሉ ማናቸውም ሥልጣንና ተግባር የክልሉ መንግሥት ይሆናል።

www.abyssinialaw.com

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ክልላዊ መንግሥቱ፡

ሀ/ የክልሉን የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ዕቅድ ያወጣል ፤ ያስፈጽማል፤

ለ/ የክልሉን ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጎችን ያወጣል፤ ያስፈጽማል፤

ሐ/ የፌዴራሉ መንግሥት በሚያወጣው ሕግ መሠረት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ያስተዳድራል፤

መ/ ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር ያዋቅራል፤ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባል። የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥትንና ይህንን ሕገ መንግሥት ይጠብቃል፤ ይከላከላል፤

ሠ/ የክልሉን ሠራተኞች አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ሕግ ያወጣል፤ ያስፈጽማል፤ ይህን በሚያስፈጽምበት ጊዜ የሀገሪቱን የትምህርት፣ የሥልጠናና የልምድ መመዘኛዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፤

ረ/ የክልሉን ፖሊስ ኃይል ያደራጃል፤ ይመራል፤ የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ይጠብቃል፤

ሰ/ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 28 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በሕግ መሠረት ምህረት ወይም ይቅርታ ያደርጋል፤

ሸ/ ለክልሉ በተወሰነው የገቢ ምንጭ ግብርና ሌሎች ታክሶችን ይጥላል፤ ይሰበስባል፤ የክልሉን በጀት ያዘጋጃል፣ ያፀድቃል፣ ያስተዳድራል፤

www.abyssinialaw.com

ቀ/ በክልሉ መንግሥት ሠራተኞችና በድርጅት ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፣

በ/ የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

ተ/ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፣

ቸ/ በክልሉ በግል ባለቤትነት ሥር ካሉ ቤቶችና ከሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፣ በክልል መንግስት ባለቤትነት ሥር ካሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ይሰበስባል፣

ኀ/ በክልሉ መንግስት ባለቤትነት ሥር በሚገኙ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ ይጥላል፣ ይሰበስባል፣

ነ/ ከፌዴራሉ መንግሥት ጋር፦

(i) በጋራ ከሚያቋቁማቸው የልማት ድርጅቶች የሚገኘውን የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክስ በሕግ መሠረት ይከፈላል፣

(ii) ከድርጅቶች የንግድ ትርፍ ላይና ከባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክስ በሕግ መሠረት ይከፈላል፣

(iii) ከከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና ከማንኛውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች የሚገኘውን የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በሕግ መሠረት ይከፈላል፣

ኘ/ በክልል መስተዳድር አካላት ከሚሰጡ ፍቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

አ/ ከደን የሚገኝ የሮያሊቲ ክፍያን ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

www.abyssinialaw.com

ከ/ በክልሉ ውስጥ ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያወጣል።

## ምዕራፍ አምስት

## ስለ ጨፌ ኦሮሚያ

## አንቀጽ 48

## ስለ ጨፌ አባላት

1. የጨፌ አባላት ሁሉ አቀፍ፣ ነጻ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ በሆነና ድምጽ በሚስጥር በሚሰጥበት የምርጫ ሥርዓት በየአምስት ዓመቱ በሕዝብ ይመረጣሉ።

2. የጨፌ አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምጽ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት ይመረጣሉ።

3. የጨፌ አባላት የመላው የክልሉ ሕዝብ ተወካዮች ናቸው።ተገዥነታቸውም ፣
   - ሀ/ ለሕገ መንግስቱ
   - ለ/ ለሕዝቡና
   - ሐ/ ለራሳቸው ሕሊና ብቻ ይሆናል።

4. ማንኛውም የጨፌ አባል በጨፌው ስብሰባ በሚሰጠው ድምጽ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም፣ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም።

5. ማንኛውም የጨፌ አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለጨፌው ፈቃድ አይያዝም፣ በወንጀል አይከሰስም።

6. ማንኛውም የጨፌ አባል የመረጠው ሕዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በሕግ መሠረት ከጨፌ አባልነት ይወገዳል።

www.abyssinialaw.com

## <u>አንቀጽ 49</u>

## <u>የጨፌ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ጨፌ በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የክልሉ ሕግ አውጭ አካል ነው።

2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት እንደተጠበቀ ሆኖ ጨፌ በክልሉ የውስጥ ጉዳዮች ላይ የበላይ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት ነው።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጨፌው በተለይ የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣

ሀ/ በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የፌዴራሉን ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጎችን የማይፃረሩ ልዩ ልዩ ሕጎችን ያወጣል፣

ለ/ የሕዝቡን ብዛት፣ የክልሉን ስፋትና ማህበረ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ግምት ውስጥ በማስገባት በክልሉ ውስጥ ተጨማሪ የአስተዳደር እርከኖችን ወይም የራስ በራስ አስተዳደራዊ አካባቢዎችን ያቋቁማል፣

ሐ/ የፌዴራሉ መንግሥት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ከአጎራባች ክልላዊ መንግሥታት ጋር የሚደረገውን ስምምነት ያፀድቃል፣

መ/ ጨፌውን የሚመሩ አፈ-ጉባዔና ምክትል አፈ-ጉባዔ ይመርጣል፣ ለጨፌው ሥራ የሚያስፈልጉትን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ይሰይማል፣

ሠ/ ከጨፌ አባላት መካከል የመስተዳድሩን ፕሬዚዳንት ይመርጣል፣ የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ያፀድቃል፣

ረ/ የኦዲትና የቁጥጥር አካል ያቋቁማል፣

www.abyssinialaw.com

ሰ/ በሕጉ መሠረት ምህረት ያደርጋል፣

ሸ/ የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ለመጠበቅ የፀጥታና የፖሊስ ኀይል ያቋቁማል፤

ቀ/ የክልሉን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ዕቅዶች ያፀድቃል፤

በ/ የክልሉን መንግሥት የገቢ ምንጮች የሚመለከቱ ሕጎችን ያወጣል፤ የክልሉን በጀት ያፀድቃል፤

ተ/ ለማህበራዊ አገልግሎት መስፋፋትና ለኢኮኖሚያዊ ልማት መፋጠን አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን ያቋቁማል፤ ያደራጃል፤

ቸ/ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት እና ዋና ኦዲተሩን ይሾማል፤

ኀ/ ለክልሉ መንግሥት በተከለለው የገቢ ምንጭ ግብርና ታክስ ይጥላል፤

ነ/ የክልሉን የሠራተኛ አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎችን በተመለከተ ሕግ ያወጣል፤

ኘ/ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ (2) (ከ) መሠረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል፤

አ/ የሀገሪቱንና የክልሉን ሕገ መንግሥት፣ አዋጆችና ሌሎች ሕጎችን በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ደንቦችን ያወጣል፤

ከ/ የክልሉን ፕሬዚዳንትና ሌሎች የክልሉን መንግሥት አካላት ባለሥልጣናት ለጥያቄ ይጠራል። የክልል መስተዳደሩን ምክር ቤት አሠራር ይመረምራል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 50
## ስለ ጨፌ አመራር

1. ጨፌ የራሱ አፈ ጉባኤ ፣ ምክትል አፈ ጉባኤና እንደአስፈላጊነቱ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ይኖሩታል።

2. አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ - ጉባኤው አሸናፊ በሆነው ወይም አብላጫ ድምፅ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት/ ድርጅቶች አቅራቢነት ከአባላቱ መሃከል ይመረጣሉ።

3. አፈጉባኤው :-

ሀ/ የጨፌውን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፣ ይመራል፣

ለ/ የጨፌን ጠቅላላ ያስተዳደር ሥራዎች ይመራል፣

ሐ/ ጨፌ በአባሉቹ ላይ የወሰነውን የዲስፒሊን እርምጃ ያስፈጽማል።

4. ምክትል አፈ ጉባዔ፡-

ሀ/ በአፈ ጉባዔው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣

ለ/ አፈ ጉባዔው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

5. የአፈ- ጉባዔው ሌሎች ተግባራት በሕግ ይወሰናሉ።

## አንቀጽ 51
## የጨፌ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. ጨፌ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣

2. የጨፌ አባላት የሥራ ዘመን ለአምስት ዓመት ነው። የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሄዶ ይጠናቀቃል፣ የቀድሞው ጨፌ የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲሱ ጨፌ ሥራውን ይጀምራል።

www.abyssinialaw.com

3. የጨፌ መደበኛ ስብሰባ በማይኖርበት ወቅት አፈ ጉባዔው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። ከጨፌ አባላት መካከል ከአንድ ሶስተኛ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ ጉባዔው ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

4. የጨፌ ስብሰባ በግልፅ ይካሄዳል፤ ሆኖም ስብሰባው በዝግ እንዲካሄድ በአባላቱ ወይም በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከተጠየቀና ከጨፌ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥያቄውን ከደገፉት ዝግ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል።

## አንቀጽ 52

## የውሳኔ አሰጣጥና የአሠራር ሥነ ሥርዓቶች

1. ከጨፌ አባላት መካከል ከሁለት ሶስተኛ በላይ ፣ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤

2. ማናቸውም ውሳኔ የሚተላለፈው በጨፌ ስብሰባ ላይ በተገኙት አባላት አብላጫ ድምፅ ይሆናል።

3. ጨፌ አሠራሩንና የሕግ አወጣጥ ሂደቱን አስመልክቶ ዝርዝር ሕጐችን ሊያወጣ ይችላል።

## ምዕራፍ ስድስት

## የሕግ አስፈፃሚ አካል

## አንቀጽ 53

## የአስፈፃሚነት ሥልጣን

1. የክልላዊ መንግሥቱ ከፍተኛ የአስፈፃሚነት ሥልጣን የተሰጠው ለመስተዳድሩ ፕሬዝዳንትና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ነው።

www.abyssinialaw.com

2. የመስተዳደሩ ምክር ቤት አባላት በመንግሥት ተግባራቸው በጋራ ለሚሰጡት ውሳኔ የጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀጽ 54
## የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት አባላት

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ የቢሮ ወይም የጽሕፈት ቤት ኃላፊዎችና በሕግ በሚወሰነው መሠረት ሌሎች አባላት የሚገኙበት አካል ነው።

2. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሰብሳቢ ፕሬዝዳንት ነው።

3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነት ለመስተዳድሩ ፕሬዝዳንትና ለክልሉ ጨፌ ነው።

## አንቀጽ 55
## የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

በፌዴራሉ ሕገ መንግሥት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. በጨፌና በፌዴራሉ መንግሥት የወጡ ሕጎችና የተሰጡ ውሳኔዎች በክልሉ ውስጥ በሥራ መተርጎማቸውን ያረጋግጣል፤

2. በሕግ በሚወሰነው መሠረት የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ቁጥር ይወስናል፤ ሌሎች አስፈፃሚ አካላትንና ልዩ ልዩ ተቋማትን ያደራጃል፣ ይቆጣጠራል፤

3. የክልሉን ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፤ ለጨፌ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በሥራ ላይ ያውላል፤

www.abyssinialaw.com

4. የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፣ የሕግ ረቂቆችን ለጨፌ ያቀርባል፣ ሲፀድቁም በሥራ ላይ ያውላል፤

5. በክልሉ ውስጥ ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፣

6. ጨፌ በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት ደንቦችን ያወጣል፤

7. በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3(ኘ) ሥር ለጨፌ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ጨፌው በማይሰበሰብበት ጊዜ የጤና ችግርና ድንገተኛ የተፈጥሮ አደጋ በክልሉ ውስጥ በሚደርስበት ጊዜ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አውጥቶ በሥራ ላይ ያውላል፤

8. በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 57 ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ ቁጥር ሠ መሠረት የሚቀርቡለትን ኃላፊዎች ፣ የዞን አስተዳዳሪዎችንና ምክትል አስተዳዳሪዎችን ይሾማል፤

9. በጨፌ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 56

## የፕሬዝዳንቱ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. ፕሬዝዳንቱ አሸናፊ በሆነው ወይም አብላጫ ድምፅ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት / ድርጅቶች አቅራቢነት በጨፌ ይሰየማል።

2. በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የፕሬዝዳንቱ የሥራ ዘመን የጨፌ የሥራ ዘመን ነው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 57
## የፕሬዝዳንቱ ሥልጣንና ተግባር

1. ፕሬዚዳንቱ የክልል መስተዳድሩ ሥራ መሪና የመስተዳድሩ ምክር ቤት ሰብሳቢ ነው።

2. ፕሬዝዳንቱ ተጠሪነቱ ለጨፌ ነው።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሬዝዳንቱ፦

ሀ/ የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይወክላል፣

ለ/ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያወጣቸውን ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተፈፃሚነት ይከታተላል፣

ሐ/ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ዋና ኦዲተርና የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ለጨፌ አቅርቦ ያስፀድቃል፣

መ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ሐ/ ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጨፌ በማይሰበሰብበት ጊዜ ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን የሥራ ኃላፊዎች በጊዜያዊነት መድቦ ያሰራል፣

ሠ/ የክልሉን ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ተቋማትና በዚህ ንዑስ አንቀጽ /ሐ/ ሥር ከተዘረዘሩት ውጭ የሆኑ የክልል መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች፣ የዞን አስተዳዳሪዎችንና ምክትል አስተዳዳሪዎችን ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በማቅረብ ያሾማል፣

ረ/ የክልሉን ደህንነት ለማስጠበቅ፣ ሕግና ሥርዓትን ለማስከበር

www.abyssinialaw.com

የተቋቋሙትን የሀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

ሰ/ በክልሉ የሚገኙትን የሀን፣ የወረዳና የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤቶችን ሥራ በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ይቆጣጠራል፣

ሸ/ ስለክልሉ ሁኔታ፣ በመስተዳድሩ ምክር ቤት ስለተከናወኑት ተግባራትና ስለወደፊት ዕቅዶች ለጨፌ በየወቅቱ ሪፖርት ያቀርባል፣

ቀ/ በህግ መሠረት ይቅርታ ያደርጋል፣

በ/ ሕገ መንግሥቱን ያከብራል፣ ያስከብራል፣

ተ/ በጨፌ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 58

## የምክትል ፕሬዝዳንት ሥልጣንና ተግባር

1. ምክትል ፕሬዝዳንቱ ፣

ሀ/ በፕሬዝዳንቱና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣

ለ/ ፕሬዝዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

2. የምክትል ፕሬዝዳንቱ ተጠሪነት ለፕሬዝዳንቱ ነው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 59

## የፕሬዝዳንቱ ጽ/ቤት

1. ፕሬዝዳንቱ በዚህ ሕገ መንግሥት የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የራሱ ጽ/ቤት ይኖረዋል።

2. የፕሬዝዳንቱ ጽ/ቤት የመስተዳድሩ ምክር ቤት ጽ/ቤት በመሆን ጭምር ያገለግላል።

3. ጽ/ቤቱ በፕሬዝዳንቱ በሚመደብ ሀሐፊ ይመራል።

4. ሀሐፊው ፣ ተጠሪነቱ ለፕሬዝዳንቱ ሆኖ፡-

   ሀ/ ጽ/ቤቱን በሰው ኃይልና በቁሳቁስ ያደራጃል፤
   
   ለ/ የመስተዳድሩን ሰነዶች በአግባቡ ይይዛል፤ ይጠብቃል፤
   
   ሐ/ የመስተዳድሩ ምክር ቤት ቃለ ጉባዔ በሚገባ መያዙን ያረጋግጣል፤
   
   መ/ በፕሬዝዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 60

## ስለ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ተቋማት መቋቋም

የክልሉን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ሥራዎች የሚያከናውኑ፣ የሚያስተባብሩና የሚመሩ ቢሮዎች፣ ኮሚሽኖችና ሌሎች መስሪያ ቤቶች እንደ አስፈላጊነታቸው ይቋቋማሉ፤ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ ሰባት

## ስለ ፍርድ ቤቶች አወቃቀርና የዳኝነት ሥልጣን

### አንቀጽ 61

### ስለ ነፃ የዳኝነት አካል መቋቋም

1. በክልሉ ነፃ የዳኝነት አካል በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል።

2. የዳኝነት ሥልጣንን ከመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በሕግ የመዳኘት ሥልጣን ከተሰጠው ተቋም ውጭ የሚያደርግና በሕግ የተደነገገውን የዳኝነት ሥርዓት የማይከተል ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም።

### አንቀጽ 62

### ስለ ባህላዊና ሐይማኖታዊ ዳኝነት

1. በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የሃይማኖትና የባህል ፍርድ ቤቶች ሊቋቋሙ ወይም ዕውቅና ሊሰጣቸው ይችላል።

2. ይህ ሕገ መንግሥት ከመጽደቁ በፊት በመንግሥት እውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ ሐይማኖታዊና ባህላዊ የዳኝነት አካላት በዚህ ሕገ መንግሥት እውቅና አግኝተው ይደራጃሉ።

### አንቀጽ 63

### የዳኝነት ሥልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው።

2. በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማናቸውም የመንግሥት አካል፣ ባለሥልጣን ወይም ሌላ ተፅዕኖ ነፃ ነው።

www.abyssinialaw.com

3. ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ፤ ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም።

4. ማንኛውም ዳኛ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በሕግ የተወሰነው የጡረታ እድሜ ከመድረሱ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከዳኝነት ሥራው አይነሳም፤

   ሀ/ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በዳኞች የዲስፒሊን ሕግ መሠረት ጥፋት ፈፅሟል ወይም ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ብሎ ሲወስን ወይም

   ለ/ በሕመም ምክንያት ዳኛው ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲወስንና

   ሐ/ የጉባዔው ውሳኔ ለጨፌ ቀርቦ በአባላቱ አብላጫ ድምፅ ተደግፎ ሲፀድቅ።

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት አንድን ዳኛ ከዳኝነት ሥራው የሚያስነሳው ጥፋት ፈጽሟል ብሎ ጉባዔው ካመነበት ጉዳዩ በጨፌ እስኪወሰን ድረስ ከዳኝነት ሥራው ይታገዳል።

6. የማንኛውም ዳኛ የጡረታ መውጫ ጊዜ አይራዘምም።

## አንቀጽ 64
## የፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና ሥልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት አካል በጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ በዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በወረዳ ፍርድ ቤት ይደራጃል።

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡-

www.abyssinialaw.com

ሀ/ ክልላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፍተኛውና የመጨረሻው የዳኝነት ሥልጣን፣

ለ/ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣንና

ሐ/ ማንኛውም ክልላዊ ፍርድ ቤት የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖርበት በሰበር የማየት ሥልጣን ይኖረዋል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

3. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከክልላዊ ሥልጣኑ በተጨማሪ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል።

4. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል።

5. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባለው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል።

6. የወረዳ ፍርድ ቤት የክልሉ የበታችና የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት አካል ነው።

7. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት አካላቱን የሚያስተዳድርበትን በጀት ለክልሉ ጨፌ አቅርቦ ያስወስናል፤ ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል።

8. የክልሉ ጠቅላይና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በውክልና ለሚሠሩት ፌዴራላዊ የዳኝነት ተግባር ከፌዴራል መንግሥት የበጀት ማካካሻ ይሰጣቸዋል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 65

## ስለ ዳኞች አሿሿም

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት በክልሉ ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በጨፌ ይሾማሉ።

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አቅራቢነት በጨፌ ይሾማሉ።

3. የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመት ለጨፌ ከማቅረቡ በፊት የፌዴራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በዕጩዎቹ ላይ ያለውን አስተያየት መጠየቅና የተሰጠውን አስተያየት ከራሱ መግለጫ ጋር ለጨፌ የማቅረብ ኃላፊነት አለበት። ሆኖም የፌዴራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የተጠየቀውን አስተያየት በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ ጨፌ የእጩ ዳኞቹን ሹመት ያፀድቃል።

## አንቀጽ 66

## ስለ ክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ መቋቋም

1. በክልሉ ውስጥ ዳኞች በአብላጫ ድምፅ የሚወከሉበት የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ይቋቋማል።

2. የክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት የጉባኤው ሰብሳቢ ይሆናል።

3. የጉባዔው አባላት ዝርዝር እንዲሁም ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 67

## ሕገ መንግሥቱን ስለመተርጎም

1. ሕገ መንግሥታዊ ክርክር ውሳኔ የሚያገኘው ከየወረዳ ምክር ቤት በሚወከል አንድ አባል በሚሰየም የሕገ መንግስት ተርጓሚ ኮሚሽን ይሆናል።

www.abyssinialaw.com

2. ኮሚሽኑ የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በሚያቀርብለት የውሳኔ ሀሳብ ላይ መክሮ በ60 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

3. የኮሚሽኑ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል።

4. ኮሚሽኑ የራሱን ሰብሳቢና ፀሐፊ ከመካከሉ ይመርጣል። ለሥራው የሚያስፈልገውን የጽህፈት አገልግሎትና የፋይናንስ ድጋፍ ከጨፌ ያገኛል።

## አንቀጽ 68

## የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ

1. የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል።

2. የክልሉ ህገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አሥራ አንድ አባላት ይኖሩታል፤ አባላቱም የሚከተሉት ናቸው።

ሀ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት....... ሰብሳቢ፤

ለ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት........................ ምክትል ሰብሳቢ፤

ሐ/ በክልል መስተዳድር ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በክልሉ ጨፌ የሚሾሙ በሙያ ብቃታቸውና በሥነ ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ስድስት የሕግ ባለሙያዎች ............. አባላት፤

መ/ በአፈ-ጉባዔው አቅራቢነት ከጨፌ አባላት መካከል የሚሰየሙ 3 ተወካዮች............ አባላት።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 69

## የአጣሪ ጉባዔው ሥልጣንና ተግባር

1. የክልሉ ሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የሕገ - መንግሥቱ አከራካሪ ጉዳዮች የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል። በሚያደርገው ማጣራትም የክልሉን ሕገ መንግሥት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሃሳብ አዘጋጅቶ ለሕገ- መንግስት ተርጓሚ ኮሚሽን ያቀርባል።

2. ጉባዔው በክልሉ መንግሥት አካላት የሚወጡ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ በማናቸውም ሁኔታ ሲነሳናጉዳዩ በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለጉዳዮች አማካኝነት ሲቀርብለት አጣርቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለኮሚሽኑ ያቀርባል።

3. የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ በፍርድ ቤቶች ሲነሣ ጉባኤው፦

   ሀ/ የክልሉን ሕገ መንግሥት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ወዲያውኑ ይመልሳል። ሆኖም ባጣሪ ጉባዔው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማናቸውም ባለጉዳይ ይህንኑ ቅሬታውን በጽሁፍ ለኮሚሽኑ ማቅረብ ይችላል፤

   ለ/ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ የውሳኔ ሀሳብ ለኮሚሽኑ ያቀርባል። የኮሚሽኑም ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

## ምዕራፍ ስምንት

## ስለዞኖች አደረጃጀትና ሥልጣን

## አንቀጽ 70

## አወቃቀርና አሠራር

1. ዞን ከክልል ቀጥሎ የሚገኝና የተወሰኑ ወረዳዎችን የያዘ የአስተዳደር እርከን ነው።

2. እያንዳንዱ ዞን በዋና አስተዳዳሪና ምክትል አስተዳዳሪ ይመራል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 71

## የዞን አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር

1. የዞን አስተዳደር በክልሉ ውስጥ ከክልሉ መስተዳድር በታች በዞን ደረጃ የተዋቀረ አስፈፃሚ አካል ነው።

2. የዞን አስተዳደር ተጠሪነት ለክልሉ ፕሬዝዳንትና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል።

3. የዞን አስተዳደር ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

   ሀ/ በተደራጀበት ዞን ውስጥ የሚገኙትን ወረዳዎች ሥራ ያስተባብራል፣

   ለ/ በዞኑ ውስጥ የተቋቋሙትን ልዩ ልዩ መምሪያዎችና ሌሎች ተቋማት ሥራ ይደግፋል፤ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣

   ሐ/ ከአንድ ወረዳ በላይ ግልጋሎት የሚሰጡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማትን ይደግፋል፣ ያስተባብራል፣

   መ/ የዞኑን ማህበራዊ አገልግሎትና ኢኮኖሚያዊ ልማት እንቅስቃሴ እያጠና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በሥራ ላይ ያውላል፣

   ሠ/ የዞኑ ቅርሣ ቅርስና የተፈጥሮ ሀብት አስፈላጊው እንክብካቤና ጥበቃ የተደረገለት መሆኑን ያረጋግጣል፣

   ረ/ የዞኑን የሥራ እንቅስቃሴ እየተከታተለ በዋና አስተዳዳሪው አማካኝነት ለፕሬዝዳንቱ ሪፖርት ያደርጋል፣

   ሰ/ በዞኑ ውስጥ ሕግና ሥርዓት መከበሩንና የሕዝቡ ሠላምና ደህንነት መጠበቁን ያረጋግጣል፣

www.abyssinialaw.com

ሸ/ በጨፌና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች በዞኑ ውስጥ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

ቀ/ በፕሬዝዳንቱና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 72

## የዞን ዋና አስተዳዳሪ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. የዞን ዋና አስተዳዳሪ በፕሬዝዳንቱ አቅራቢነት በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሾማል።

2. የዞን ዋና አስተዳዳሪ የሥራ ዘመን በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የፕሬዝዳንቱ የሥራ ዘመን ይሆናል።

## አንቀጽ 73

## የዞን ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

1. የዞን ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነት ለፕሬዝዳንቱ ሆኖ በዞኑ ውስጥ የአስተዳደሩ የበላይ ሥራ መሪ ነው።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የዞን ዋና አስተዳዳሪ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

   ሀ/ ፕሬዝዳንቱን ወክሎ ዞኑን ያስተዳድራል፣ ሥራውን በበላይነት ይመራል፤

   ለ/ በዞኑ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ መምሪያዎችና ተቋማት እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ሥራቸውን ያስተባብራል፣ ሪፖርት ይቀበላል፤ ድጋፎችን ይሰጣል፤

www.abyssinialaw.com

ሐ/ የአካባቢውን ሠላምና ደህንነት ለመጠበቅ በዞኑ ውስጥ ሕግና ሥርዓትን እንዲያስከብሩ የተቋቋሙትን የዐጥታና የፖሊስ ኃይሎችን በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

መ/ በዞኑ ውስጥ የሚገኙ የሌሎች የአስተዳደር እርከኖችን ሥራ ያስተባብራል፤

ሠ/ የዞኑን የሥራ እንቅስቃሴ እየተከታተለ በየጊዜው ለፕሬዝዳንቱና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል፤

ረ/ በፕሬዝዳንቱና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 74

## የዞን ምክትል አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

1. የዞን ምክትል አስተዳዳሪ ፦

ሀ/ ዋና አስተዳዳሪው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

ለ/ በዋና አስተዳዳሪው ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

2. የምክትል አስተዳዳሪው ተጠሪነት ለዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ነው።

## አንቀጽ 75

## የዞን አስተዳደር ጽ/ቤት

1. የዞን አስተዳደር ጽህፈት ቤት ተጠሪነቱ ለዋና አስተዳዳሪው ሆኖ አንድ ኃላፊ ይኖረዋል።

www.abyssinialaw.com

2. በዚህ ሕገ መንግሥት የፕሬዚዳንቱን ጽህፈት ቤት ኃላፊ በሚመለከት የተደነገገው የዞን አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ኃላፊውን ተግባርና ኃላፊነት በተመለከተም እንደአግባብነቱ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## ስለ ወረዳ አደረጃጀትና ሥልጣን

### አንቀጽ 76

### አደረጃጀት

ወረዳ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል።

1. የወረዳ ምክር ቤት
2. የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤትና
3. የወረዳ ዳኝነት አካል

### አንቀጽ 77

### ስለ ወረዳ ምክር ቤት

1. የወረዳ ምክር ቤት ከጨፌ ኦሮሚያ በታች የሚደራጅ አካል ነው።

2. የወረዳው ምክር ቤት፡-

ሀ/ በሥሩ ከተደራጁ ቀበሌዎች በሚወከሉ የሕዝብ ተመራጮች የሚቋቋም ነው፤

ለ/ ከአባላቱ መካከል አሸናፊ በሆነው ወይም አብላጫ ድምጽ ባገኘው ወይም ባገኙት የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች አቅራቢነት የሚሰየሙ አፈጉባኤና ምክትል አፈጉባኤ ይኖሩታል።

ሐ/ እንዳስፈላጊነቱ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ሊያዋቅር ይችላል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 78

## የወረዳ ምክር ቤት አባላት አመራረጥና ተጠሪነት

1. የወረዳ ምክር ቤት አባላት በወረዳው ውስጥ ከሚገኙት የቀበሌ ነዋሪዎች መካከል በቀጥታ በሕዝብ ይመረጣሉ።

2. የወረዳ ምክር ቤት አባላት ተጠሪነት ለመረጣቸው ሕዝብ ይሆናል።

## አንቀጽ 79

## የወረዳ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የወረዳ ምክር ቤት የወረዳው ከፍተኛ የሥልጣን አካል ነው።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

   ሀ/ የወረዳውን ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶችና አስተዳደራዊ የሥራ እቅዶችና ፕሮግራሞችን ረቂቅ መርምሮ ያፀድቃል፤

   ለ/ በወረዳው ውስጥ መሠረታዊ የግብርና ልማት ሥራዎች ወቅቱን ጠብቀው መካሄዳቸውንና የተፈጥሮ ሃብት ልማት፣ ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት መከናወኑን ይከታተላል፤

   ሐ/ ነዋሪው ሕዝብ ለልማት ሥራ በስፋት የሚነሣሣበትንና የሚንቀሳቀስበትን አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል፤

   መ/ አብላጫ መቀመጫ ከያዘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል አፈ- ጉባኤና ምክትል አፈ-ጉባኤ ይመርጣል፤ ዋና አስተዳዳሪም ይሰይማል።

   ሠ/ በዋና አስተዳዳሪው የሚቀርቡለትን ምክትል አስተዳዳሪንና የሌሎች ኃላፊዎችን ሹመት ያፀድቃል፤

www.abyssinialaw.com

ረ/ የራሱን የአሠራር ሥነ ሥርዓት የሚወስን ውስጠ ደንብ ያወጣል፤

ሰ/ በሕግ በተወሰነው መሠረት የመሬት መጠቀሚያ ታክስ፣ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብርና ሌሎች የአገልግሎት ታክሶችን ክፍያዎች መሰብሰባቸውን ያረጋግጣል፤

ሸ/ ክልሉ ከሚመድበውና ከሚያስተዳድረው ውጭ ያለውን የወረዳውን ገቢ ምንጭ በአግባቡ ይጠቀማል፤ በጀቱንም መርምሮ ያፀድቃል፤

ቀ/ አግባብ ያላቸውን የክልሉን መንግሥት አካላት አስተያየት በመጠየቅ ከወረዳው አስተዳደር ውጭ የሆኑ ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ይሾማል፤

በ/ የወረዳውን ሠላምና ፀጥታ ለማረጋገጥ የሚያስችል መመሪያ አውጥቶ በሥራ ላይ ያውላል።

## አንቀጽ 80
## ስለ ወረዳ ምክር ቤት አፈጉባኤ

1. አፈጉባኤው ምክር ቤቱን ለስብሰባ የመጥራትና የመምራት ኃላፊነት ይኖርበታል።

2. በዚህ ሕገ - መንግሥት ለክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንዳስፈላጊነታቸው ለወረዳው ምክር ቤት አፈጉባኤ ተፈፃሚ ይሆናል።

## አንቀጽ 81
## የወረዳ ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ

1. ምክትል አፈ ጉባኤው በምክር ቤቱ አፈጉባኤ ተለይተው የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

2. አፈ ጉባኤው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 82

## የወረዳው ምክር ቤት የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የወረዳ ምክር ቤት በየሶስት ወሩ ይሰበሰባል።

2. ከአባላቱ መካከል ከሁለት ሶስተኛ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤ ውሣኔ የሚተላለፈው በአብላጫ ድምፅ ይሆናል።

3. የወረዳ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል። የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ከማብቃቱ አንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሄዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞው ምክር ቤት ሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።

4. የወረዳ ምክር ቤት ስብሰባ በግልፅ ይካሄዳል። ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማይኖርበት ወቅት አፈ-ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። ከአባላቱ መካከል ግማሽ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲካሄድ ከጠየቁ አፈጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

## አንቀጽ 83

## ስለ ወረዳ ምክር ቤት ጽ/ቤት

የወረዳ ምክር ቤት የራሱ ጽ/ቤት ሊኖረው ይችላል።

## አንቀጽ 84

## ስለ ወረዳ አስተዳደር ም/ቤት

1. የወረዳ አስተዳደር ም/ቤት የወረዳው ሕግ አስፈፃሚ አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለዋና አስተዳዳሪውና ለወረዳው ምክር ቤት ነው።

2. የወረዳ አስተዳደር ም/ቤት የወረዳው አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪ፣ እንዲሁም በወረዳው ውስጥ የተቋቋሙ ዋና ዋና አስፈፃሚ የሴክተር መስሪያ ቤቶች ኃላፊዎች የሚገኙበት አካል ነው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 85

## ስለ ወረዳ አስተዳደር ም/ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የወረዳ አስተዳደር ም/ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

ሀ/ የመንግሥት ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ መመሪያዎች፣ እቅዶችና ፕሮግራሞች በወረዳ ውስጥ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

ለ/ በወረዳው ውስጥ የሚገኙ አስፈፃሚ አካላትን በበላይነት ያስተባብራል፤ ሥራቸውን ይከታተላል፣ ይመራል፤

ሐ/ የወረዳውን ዓመታዊ በጀት ረቂቅ ያዘጋጃል፤ ለወረዳው ምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲፀድቅም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

መ/ የወረዳውን ሠላምና ፀጥታ ይጠብቃል፤ የወረዳውን የፀጥታና የፖሊስ አካላት ይመራል፣ ሥራቸውን ያስተባብራል፤

ሠ/ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ እቅዶችን አዘጋጅቶ ለወረዳው ምክር ቤት በማቅረብ ያስፀድቃል፤

ረ/ የተፈጥሮ ሃብትን ይጠብቃል፤ ያለማል፤ ይንከባከባል፤ ሕዝቡን ለልማት ሥራ በስፋት ያንቀሳቅሳል፤

ሰ/ በወረዳው ውስጥ የሚገኝ ቅርሳ ቅርስ አስፈላጊው ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገለት መሆኑን ይከታተላል፤

ሸ/ በወረዳው ምክር ቤትና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

2. የወረዳ አስተዳደር ም/ቤት አባላት በመንግሥታዊ ሥልጣናቸው ለሚፈጽሙት ተግባርና ለሚያሳልፉት ውሳኔ በጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 86

## ስለ ወረዳው ዋና አስተዳዳሪ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ከወረዳው ምክር ቤት መካከል አሸናፊ በሆነው ወይም አብላጫ ድምፅ ባገኘው ወይም ባገኙት የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት በወረዳው ምክር ቤት ይሰየማል።።

2. በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የወረዳው አስተዳዳሪ የሥራ ዘመን የወረዳው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

## አንቀጽ 87

## የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

1. የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነት ለወረዳው ምክር ቤትና ለፕሬዝዳንቱ ሆኖ የወረዳው አስተዳደር ሥራ መሪ ነው።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳዳሪው

   ሀ/ የወረዳውን አስተዳደር ም/ቤት ይመራል፤

   ለ/ የመንግሥት ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ መመሪያዎችና ፕሮግራሞች በወረዳው ውስጥ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

   ሐ/ የወረዳውን አስተዳደር ም/ቤት አባላት፣ ልዩ ልዩ ተቋማትንና በሥሩ የሚገኙትን ቀበሌዎች ሥራ በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

   መ/ የወረዳው ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ የኢኮኖሚያዊ ልማት ፕሮግራሞች እና እቅዶች ወቅቱን ጠብቀው መዘጋጀታቸውን ይቆጣጠራል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

www.abyssinialaw.com

ሠ/ የወረዳውን ሕግና ሥርዓት እንዲያስከብሩ የተቋቋሙትን የዐጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

ረ/ ለወረዳው ምክር ቤትና ለዞን አስተዳደር በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፤

ሰ/ በወረዳው ምክር ቤትና በክልሉ ፕሬዝዳንት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 88

## የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

1. የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ ፦

   ሀ/ ዋና አስተዳዳሪው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፡

   ለ/ በወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

2. የወረዳው ምክትል አስተዳዳሪ ተጠሪነት ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ይሆናል።

## አንቀጽ 89

## የወረዳ አስተዳደር ም/ቤት ጽ/ቤት

1. የወረዳ አስተዳደር ም/ቤት ጽ/ቤት በዋና አስተዳዳሪው ተመርጦ በሚመደብ አንድ የሥራ ኃላፊ ይመራል።

2. በዚህ ሕገ መንግሥት የፕሬዝዳንቱን ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት በሚመለከት የተደነገጉት እንደ አግባብነታቸው ለወረዳው አስተዳደር ም/ቤት ጽ/ቤትም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

www.abyssinialaw.com

# ምዕራፍ አሥር

# ስለ ቀበሌ አደረጃጀትና ሥልጣን

## አንቀጽ 90

## አደረጃጀት

ቀበሌ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፤

1. የቀበሌ ምክር ቤት፤
2. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት እና
3. የማህበራዊ ፍርድ ቤት።

## አንቀጽ 91

## ስለቀበሌ ምክር ቤት

1. የቀበሌ ምክር ቤት በቀበሌው ውስጥ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ነው።
2. የቀበሌ ምክር ቤት አባሎች በቀጥታ በቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ የሚመረጡ ይሆናሉ።
3. የቀበሌው ምክር ቤት ተጠሪነት ለቀበሌው ሕዝብና ለወረዳው ምክር ቤት ይሆናል።

## አንቀጽ 92

## የቀበሌ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

ቀበሌ ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. የወረዳው ምክር ቤትና አስተዳደር ምክር ቤት የሚያወጧቸውን እቅዶችና መመሪያዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

www.abyssinialaw.com

2. መመሪያዎችን ያወጣል፣ በሥራ ላይም እንዲውሉ ያደርጋል፤

3. ከቀበሌው ሕዝብ መካከል የቀበሌውን አስተዳዳሪ ይሰይማል፣ የቀበሌውን አስተዳደር ምክር ቤትም ያደራጃል፤

4. በቀበሌው አስተዳዳሪ የሚቀርቡለትን የቀበሌውን ምክትል አስተዳዳሪና የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመት ያፀድቃል፤

5. የማህበረ - ኢኮኖሚያዊ ልማትና አስተዳደራዊ እቅዶችንና ፕሮግራሞችን መሠረት በማድረግ የሥራ አፈፃፀም መርሃ ግብር ያወጣል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

6. ለቀበሌው ሕዝብ የሚጠቅሙ ሌሎች ተጨማሪ እቅዶችን ያወጣል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፤

7. የቀበሌውን ሕዝብ ለልማት ሥራ ያነሳሳል፣ የተፈጥሮ ሃብትን ልማትና እንክብካቤ ሥራ ይከታተላል፤

8. በቀበሌው ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል።

## አንቀጽ 93

## ስለ ቀበሌ ምክር ቤት አፈጉባኤና ምክትል አፈጉባኤ

1. የቀበሌ ምክር ቤት ከአባላቱ መካከል አሸናፊ በሆነው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች ወይም አብላጫ ድምፅ ባገኙት አቅራቢነት በቀበሌው ምክር ቤት በሚሰየሙ አፈጉባኤና ምክትል አፈጉባኤ ይመራል።

2. አፈ ጉባኤው ምክር ቤቱን ይሰበስባል፣ ይመራል፣ አጀንዳዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ቃለ ጉባኤ እና ሰነዶች በአግባቡ መያዛቸውን ይቆጣጠራል።

www.abyssinialaw.com

3. ምክትል አፈጉባኤው በአፈጉባኤው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤ አፈጉባኤው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

## አንቀጽ 94
## የቀበሌው ምክር ቤት የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የቀበሌው ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባውን በወር አንድ ጊዜ ያካሄዳል።

2. ከአባላት መካከል ከሁለት ሶስተኛ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤ ውሳኔ የሚተላለፈው በአብላጫ ድምፅ ይሆናል።

3. የቀበሌው ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል። የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።

## አንቀጽ 95
## የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አወቃቀር

1. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪና በሕግ የሚወሰኑ ሌሎች አባላት የሚገኙበት የበታች አስፈፃሚ አካል ነው፤

2. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ተጠሪነት ለቀበሌው ምክር ቤትና ለወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት ይሆናል።

3. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በግልና በወል የቀበሌውን አስተዳደር ሥራ ይመራሉ፤ ያስተባብራሉ።

4. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በምክር ቤት አባልነታቸው ለሚሰጡት ውሳኔና ለሚፈፅሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 96
## የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

   ሀ/ የቀበሌው አስተዳደር ምክር ቤት፣ የልማት ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ይነድፋል፤ ለቀበሌው ምክር ቤት በማቅረብ ያስፀድቃል፤ ሥራ ላይም ያውላል፤

   ለ/ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ እንክብካቤና ልማት ሥራ እንዲካሄድ ያደርጋል፤ ሕዝቡንም ለልማት ሥራ ያነሳሳል፤ ያስተባብራል፤

   ሐ/ የቀበሌው ሠላምና ፀጥታ እንዲጠበቅ ያደርጋል፤

   መ/ በአካባቢው ለሚገኙት ቅርሳ ቅርሶች ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ ያደርጋል፤ በጥቅም ላይ ስለሚውሉበት መንገድም አግባብ ላለው አካል ያሳውቃ፤

   ሠ/ ለቀበሌው ምክር ቤት በየወቅቱ የሥራ ሪፖርት ያቀርባል፤

   ረ/ በቀበሌው ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

2. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት የሥራ ዕቅዶቹን የሚነድፈውና አፈፃፀማቸውን የሚገመግመው እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው እየተገናኘ ይሆናል።

## አንቀጽ 97
## ስለ ቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ከቀበሌው ምክር ቤት መካከል አሸናፊ በሆነው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች ወይም አብላጫ ድምፅ ባገኙት አቅራቢነት በቀበሌው ምክር ቤት ይሰየማል።

2. በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የቀበሌ አስተዳዳሪው የሥራ ዘመን የቀበሌው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 98
## የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

1. የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነት ለቀበሌው ምክር ቤትና ለወረዳው አስተዳደሪ ይሆናል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌው አስተዳዳሪ ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

   ሀ. የቀበሌውን አስተዳደር ምክር ቤት ይሰበስባል፤ ይመራል፤

   ለ. ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ዕቅዶች በቀበሌው በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

   ሐ. ዕጩ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞችን ለቀበሌው ምክር ቤት አቅርቦ ያሾማል፤

   መ. ለቀበሌው ምክር ቤት፣ ለነዋሪው ሕዝብና ለወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት የሥራ ሪፖርት ያቀርባል፤

   ሠ. በቀበሌው አስተዳደር ምክር ቤት፣ በቀበሌው ምክር ቤትና በወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 99
## ,የቀበሌ ምክትል አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

1. የቀበሌ ምክትል አስተዳዳሪ ከቀበሌው ነዋሪዎች መካከል በቀበሌው አስተዳዳሪ አቅራቢነት በምክር ቤቱ የሚሰየም ይሆናል።

2. ምክትል አስተዳዳሪው፡-

   ሀ/ ዋናው አስተዳዳሪ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

   ለ/ በቀበሌው አስተዳዳሪ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

3. የምክትል አስተዳዳሪው ተጠሪነት ለቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ ይሆናል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 100
## ስለቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት

የቀበሌው ጽ/ቤት በበላይነት የሚመራው በቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ ይሆናል።

## አንቀጽ 101
## የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት

1. የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት በዚህ ህገ-መንግሥት ተቋቁሟል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

2. የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች በዚህ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 98 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሐ) መሠረት ይሾማሉ።

3. የማህበራዊ ፍርድ ቤት የሥራ ዘመን የቀበሌው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

## ምዕራፍ አሥራ አንድ
## የክልሉ ፖሊሲ ዓላማዎች
## አንቀጽ 102
## ዓላማዎች

1. ማንኛውም የመንግሥት አካል የፌዴራሉንና የክልሉን ህገ-መንግሥት፣ ሌሎች ህጎችና ፖሊሲዎች በሥራ ላይ ሲያውል በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት ዓላማዎች ላይ መመስረት አለበት።

2. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ "መንግሥት" ማለት የኦሮሚያ ክልል መንግሥት ማለት ነው።

## አንቀጽ 103

## ፖለቲካ ነክ ዓላማዎች

1. መንግሥት በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመስረት ሕዝቡ በሁሉም ደረጃዎች ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት።

www.abyssinialaw.com

2. መንግሥት የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ማንነት የሚያከብርና በዚሁ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸው እኩልነትን፣ አንድነትንና ወንድማማችነትን የማጠናከር ግዴታ አለበት።

## አንቀጽ 104
## ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች

መንግሥት፦

1. ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች በክልሉ በተጠራቀመ ዕውቀትና ሀብት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ኃላፊነት አለበት፤

2. የክልሉ ነዋሪዎች የኢኮኖሚ ሁኔታቸውን ለማሻሻል እኩል ዕድል እንዲኖራቸው ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፤

3. በኢኮኖሚያዊና በማኅበራዊ እድገት ወደ ኋላ ለቀሩ አካባቢዎች ልዩ ድጋፍ ያደርጋል፤

4. የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ እንዳይደርስ መከላከልና አደጋው ሲደርስም ለተጎጂው ዕርዳታ በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ አለበት፤

5. መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን በሕዝብ ስም በይዞታው ሥር በማድረግ ለህዝቡ የጋራ ጥቅምና ዕድገት እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤

6. የክልሉ ልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ሲዘጋጁ ሕዝቡ በየደረጃው እንዲሳተፍ ማድረግ አለበት፤ የሕዝቡንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት፤

7. የሕዝቡን ዕውቀት፣ ጉልበትና ገንዘብ በማቀናጀት ፈጣን ልማት የሚረጋገጥበትን መንገድ መቀየስ አለበት፤ ሕዝቡ በክልሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሚና እንዲኖረው ማድረግ አለበት፤ ስለሆነም ሕዝቡ ዕቅዶችና ፖሊሲዎችን በመንደፍ ብቻ ሳይሆን በማስፈፀምና በመገምገም መሳተፍ አለበት፤

8. በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች እኩል የሚሳተፉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት፤

www.abyssinialaw.com

9. የሠራተኛውን ሕዝብ ጤንነት፣ ደህንነትና የኑሮ ደረጃ ለመጠበቅ መጣር አለበት።

## አንቀጽ 105
## ማህበራዊ ነክ ዓላማዎች

1. መንግሥት የአገሪቱና የክልሉ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንፁህ ውሃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና የማህበራዊ ዋስትና እንዲኖራቸው ያደርጋል።

2. ትምህርት በማናቸውም ረገድ ከኃይማኖት፣ ከፖለቲካ አመለካከቶችና ከባህላዊ ተፅዕኖዎች ነፃ በሆነ መንገድ መካሄድ አለበት።

## አንቀጽ 106
## ባህል ነክ ዓላማዎች

1. የክልሉ መንግሥት መሠረታዊ መብቶችንና ሰብዓዊ ክብርን፣ ዲሞክራሲንና ህገ-መንግሥቱን የማይቃረኑ ባህሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት።

2. የተፈጥሮ ሀብቶችንና የታሪክ ቅርሶችን መጠበቅ የመንግሥትና የሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች ግዴታ ነው።

3. የክልሉ መንግሥት አቅም በፈቀደ መጠን ኪነ ጥበብን፣ ሳይንስንና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ግዴታ አለበት።

## አንቀጽ 107
## የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች

1. መንግሥት ሁሉም የክልሉ ነዋሪ ንፁህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው የመጣር ኃላፊነት አለበት።

2. ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማት ዕርምጃ የአካባቢውን ደህንነት የማያናጋ መሆን አለበት።

www.abyssinialaw.com

3. የሕዝብን የአካባቢ ደህንነት የሚመለከት ፖሊሲና ፕሮግራም በሚነደፍበትና ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ሕዝቡ ሃሳቡን እንዲገልፅ መደረግ አለበት።

4. መንግሥትና የክልሉ ነዋሪዎች አካባቢያቸውን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው።

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 108
### የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ

1. ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት እና ጨፌ በማይሰበሰብበት ጊዜ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በዚህ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 55/ን0ሰ አንቀጽ 7 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ያስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ያወጣል።

2. የመስተዳድር ምክር ቤቱ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌውን አውጥቶ በሥራ ላይ በዋለ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ አፈ ጉባዔው ጨፌን በአስቸኳይ ስብሰባ ጠርቶ ማስፀደቅ አለበት።

3. የመስተዳድሩ ምክር ቤት ያወጣው የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በጨፌ ተቀባይነት ካገኘ ሊቆይ የሚችለው ለስድስት ወራት ብቻ ይሆናል። ሆኖም የክልሉ ጨፌ በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ሲወስን የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌው በየአራት ወሩ ሊታደስ ይችላል።

4. የመስተዳድሩ ምክር ቤት እና ጨፌ በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ የሚያወጣቸው ድንጋጌዎችና የሚወስዷቸው ዕርምጃዎች በማናቸውም ረገድ በዚህ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 15፣16፣ 18/1/ እና /2/ ፣ 21 /1/፣ 24/1/ 25፣ 27/1/ እና 39 የተቀመጡትን መብቶች የሚገድቡ መሆን የለባቸውም።

### አንቀጽ 109
### የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ

1. በክልሉ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በሚታወጅበት ወቅት ጨፌ ከአባላቱና ከህግ ባለሙያዎች መርጦ የሚመድባቸው ሰባት አባላት ያሉት የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ

www.abyssinialaw.com

አፈጻፀም መርማሪ ቦርድ ያቋቁማል። ቦርዱ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌው በጨፌ በሚፀድቅበት ጊዜ ይቋቋማል።

2. የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

ሀ. በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ምክንያት የታሰሩትን ግለሰቦች ስም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይፋ ማድረግና የታሰሩበትን ምክንያት መግለፅ፣

ለ. በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ወቅት የሚወሰዱት ዕርምጃዎች በማናቸውም ረገድ ኢሰብዓዊ አለመሆናቸውን መቆጣጠር፣

ሐ. ማናቸውም የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ዕርምጃ ኢሰብአዊ መሆኑን ሲያምንበት የመስተዳድሩ ፕሬዚዳንት ወይም የመስተዳድሩ ምክር ቤት እርምጃውን እንዲያስተካክል ሃሳብ መስጠት፣

መ. የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ እንዲቀጥል ለጨፌ ጥያቄ ሲቀርብ ያለውን አስተያየት ማቅረብ።

## አንቀጽ 110
## የክልሉ ዋና ኦዲተር

1. የክልሉ ዋና ኦዲተር በመስተዳድሩ ፕሬዚዳንት አቅራቢነት በጨፌ ይሾማል።
2. የክልሉ ዋና ኦዲተር የክልሉን ቢሮዎችና የሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሂሳቦችን በመቆጣጠር በጨፌ የተመደበው ዓመታዊ በጀት በበጀት ዓመቱ እንዲሰሩ ለተወሰኑ ሥራዎች በሚገባ መዋሉን ለጨፌ ሪፖርት ያቀርባል።
3. የክልሉ ዋና ኦዲተር የመሥሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለጨፌ አቅርቦ ያስፀድቃል።
4. የዋና ኦዲተር ተጠሪነት ለጨፌ ይሆናል።
5. የዋናው ኦዲተር ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር በህግ ይወሰናል።